# የኢንቨስተሮች ጥበቃ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ

# ክፍል 2

በባለፈው ሳምንት ጽሁፍ የኢንቨስተሮች ጥበቃ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በሚል ርዕስ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት በመጀመሪያ ለኢንቨስተሮች በምን አይነት መልኩ ጥበቃ እንደሚያደርጉ አይተናል። በተጨማሪ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ኢንቨስተሩ ላይ የሚደርሱ ጥፋቶችን በማየት እና ውሳኔ በመስጠት ረገድ ምን አይነት ሚና እንደሚጫወት ተመልክተናል። በማስከተል ደግሞ ሌሎች የኢንቨስተር ጥበቃ አሰራሮች ምን እንደሚመስል በዝርዝር ለመቃኘት እንሞክራለን። በዚህ ጽሁፍ ከላይ በተጠቀሱ ተቋማት የተዘረጉ የኢንቨስተር ጥበቃ የህግ እና የአሰራር ዘዴዎች በተጨማሪ ኢንቨስተሩ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥፋቶችን እንዴት ልንከላከል ይገባል የሚለውን እና ይህን ተከትሎ የሚነሱ ግጭቶች በምን አይነት መልኩ ሊፈቱ እንደሚችሉ እናያለን።

1. **የግልግል ዳኝነት**

የግልግል ዳኝነት የኢንቨስተር ጥበቃ ዋንኛ መሳሪያ ነው። የካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 111 ከግብይቶች ለሚነሱ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ በግልጽ ያበረታታል። በዚህም መሰረት በኢንቨስተሮች እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች መካከል የሚደረጉ ስምምነቶች የግልግል ዳኝነትን ድንጋጌዎች ማካተት አለባቸው።

> "የውስጥ ቅሬታ አፈታት ዘዴዎችን መዘርጋት ሌላኛው የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴ ነው።"

የግልግል ዳኝነት ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር በተለምዶ ፈጣን እና ሚስጥራዊ ሆኖ ለጉዳዩ እልባት ከመስጠት ባሻገር ተዋዋይ ወገኖች የፋይናንስ እና የተለያዩ እውቀት ያላቸውን የግልግል ዳኞች በሂደቱ ለማሳተፍ እንዲመርጡ ያስችላቸዋል። የግልግል ዳኞችም የሚሰጡት ውሳኔ እንደተዋዋይ ወገኖች ስምምነት አስገዳጅ ባህሪው ያለው የመጨረሻ ውሳኔ ሊሆን ይችላል።

2. **የውስጥ ቅሬታዎች አፈታት ዘዴዎች**

የውስጥ ቅሬታ አፈታት ዘዴዎችን መዘርጋት ሌላኛው የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴ ነው። ለሕዝብ የሚሸጡ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግውዝ አልባ ማድርግ መመሪያ አንቀጽ 12 አውጪዎች የኢንቨስተሮች ቅሬታዎችን እንዲቀበሉ እና በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ እልባት እንዲሰጡ፣ መደበኛ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ሂደትን እንዲዘረጉ ግዴታ ይጥልባቸዋል። ይህ የቅሬታ አፈታት ዘዴ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግውዝ አልባ የማድረግ ሂደት ውስጥ ከባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ ስህተት ያጋጠማቸው ኢንቨስተሮች ፈጣን እና ዝቅተኛ በሆነ ወጪ ችግሩ የሚፈታበት አሰራር ያቋቁማል።

3. **ደጋፊ ተቋማት**

የኢንቨስተር ጥበቃ ሥራ በሌሎች ተቋማት የሚደገፍ ሲሆን ከስር የተጠቀሱ ተቋማት በተዘዋዋሪ ወሳኝ የኢንቨስተር መከላከያ ሚና የሚጫወቱ ናቸው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal

**ፈቃድ ያላቸው ኦዲተሮች እና የኦዲት ቁጥጥር አካል፡-** በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የተዘረዘሩ ኩባንያዎች የፋይናንስ መግለጫዎቻቸውን በገለልተኛ እና በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በተመዘገበ የኦዲት ድርጅት እንዲመረመሩ መደረጉ አስተማማኝ የሆነ ይፋ የማውጣት የአሰራር ሥርዓት ነው። ውጤታማ የኦዲት ቁጥጥር አካል የእነዚህን ኦዲቶች ጥራት እና ታማኝነት ያረጋግጣል፣ ይህም የኦዲት ብልሹ፣ ሃሰተኛ እና ድብቅ አሰራር እና ሁነቶችን ይከላከላል።

**የኮርፖሬት አስተዳደር ማዕቀፍ፡** ባለሥልጣኑ ለካፒታል ገበያ ተዋናዮች የኮርፖሬት አስተዳደርን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ማውጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች መመሪያ እና የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ውስጠ ደንብ በዚህ ዙሪያ ቁልፍ መርሆችን አካተዋል። የአናሳ ባለአክሲዮኖችን መብቶች መጠበቅ፣ የቦርድ ገለልተኝነትን ማረጋገጥ፣ ተዛማጅ ወገን ግብይቶችን መቆጣጠር የመሰሉት በተወሰኑ የውስጥ አካላት የሚደረግ ብዝበዛ የሚከላከሉ የአስተዳደር መሳሪያዎች ናቸው።

**የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፡** በካፒታል ገበያው የሚደረጉ ግብይቶች ለገንዘብ ማጠቢያ ወይም ለሽብርተኝነት በገንዘብ ለመርዳት ጥቅም ላይ እንዳይውል ለመከላከል ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ጋር መተባበር ወሳኝ ነው። የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች "ደንበኛዎን ይወቁ" በሚል ደንበኞቻቸውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሂሳብ በሚከፍቱበት ወቅት የሚያስሞሏቸው መጠይቆች የደንበኞቻቸውን የገንዘብ ምንጭ ጨምሮ ዝርዝር መረጃ ለማወቅ የሚረዱ በመሆናቸው ሂደቶቹ የፋይናንስ ደህንነትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ናቸው። ይህ ሁለት ዓላማ ያለው ነው፣ የመጀመሪያው የገንዘብ ወንጀልን ለመዋጋት የሚጠቅሙ ሲሆን በተጨማሪ የኢንቨስተሮችን ማንነት ለማረጋገጥ ይረዳሉ፣ይህንንም በማድረግ የካፒታል ገበያን ደህንነት ሽፋን ይጨምራሉ።

**ንቁ የፋይናንስ ሚዲያ እና የሲቪል ማህበረሰብ፡** ገለልተኛ የፋይናንስ ጋዜጠኝነት፣ የተንታኝ ሪፖርቶች እና የኢንቨስተሮች ተሟጋች ቡድኖች እንደ መደበኛ ያልሆኑ የኢንቨስተር ጠባቂዎች ሆነው ያገለግላሉ፣ የኩባንያዎችን ይፋ የማድረግ ግዴታ እና የግብይት ተግባራትን ይመረምራሉ፣ በዚህም የምርመራ ውጤት ላይ ተመስርቶ ተቋማትን ተጠያቂ ያደርጋሉ።

## 4. የኢትዮጵያ የኢንቨስተር ጥበቃ ሞዴል ጥንካሬዎች

የኢትዮጵያ የኢንቨስተር ጥበቃ የህግ ማዕቀፍ ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎቸን እና ልምዶች ጋር የሚጣጣሙ በርካታ ጠንካራ ጎኖች አሉት። ይህ የሆነበት ምክንያት የካፒታል ገበያን ቀይተን መጀመራችን የራሱ የሆነ ተጽዕኖ አሳድሮ ያለፈ ቢሆንም በሌላ አግባብ ከሌሎች ሃገራት ካፒታል ገበያዎች ተግዳሮቶችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም እድል የሚሰጥ ነው። ሃገራችን ይህን እድል በመጠቀም ጠንካራ የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ዘርግታለች።

**አጠቃላይ የህግ መሰረት፡** አዋጁ እና ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች ለእያንዳንዱ የካፒታል ገበያ ተቋማት ግልጽ የስልጣን ተዋረድ ያለው የህግ መሰረት ሰጥቷል።

**የአደጋ ስጋት ቅነሳ፡** በፈቃድ አሰጣጥ፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ ሂደት እንዲሁም የኢንቨስተሮችን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገንዘብ እና ንብረት ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች ሀብት ለይቶ መያዝ ጋር በተገናኝ ትኩረት ሰጥቶ ቁጥጥር ማድረጉ በኢንቨስተሮች ጥበቃ ዙሪያ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ዋና ዋና አደጋዎችን ለመቀነስ ይረዳል። ይህ አሰራር እጅግ ጠቃሚ እና የኢንቨስተሮችን በራስ መተማመን የሚጨምር ነው።

**ተደራራቢ የቁጥጥር ሥርዓት፡** በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ሞዴል በርካታ የፍተሻ ደረጃዎችን ዘርግቷል። የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የዕለት ተዕለት የግብይት ሥራን ይከታተላል፣ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ደግሞ ሰነዶቹን የመያዝ፣ የክፍያ እና የርክክብ አገልግሎት የሚያሳልጥ ሲሆን ባለሥልጣኑ አጠቃላይ የቁጥጥር ሥራ ያከናውናል። ይህ የተደራረበ የኢንቨስተር ጥበቃ ሥራ ስርዓቱን የበለጠ ጠንካራ ያደርገዋል።

**ግጭት ፈቺ ተቋም ያለው መሆኑ፡** በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት እና ተዛማጅ ተግባራት ዙሪያ የሚነሱ አለመግባባቶች እና ክርክሮች ውስብስብ በመሆናቸው እና ለመፍታት በሙያው የበቁ ልዩ ባለሙያዎችን የሚፈልጉ በመሆናቸው ይሄንን በመገንዘብ ለካፒታል ገበያ የራሱ ፍርድ ቤት በማቋቋም ለዳኝነቱ የተለያየ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች መሾም የባለሙያን የግጭት አፈታት አስፈላጊነት እውቅና የሚሰጥ ነው።

**ጠንካራ የህግ ማስፈጸም ሥርዓት፡** ባለሥልጣኑ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን ለመቅጣት በየመመሪያዎቹ ዝርዝር የቅጣት አፈጻጸም ስርዓት የዘረጋ መሆኑ የገበያውን እና ግብይቱን ተዓማኒነት ያለው በማድረግ የኢንቨስተር ጥበቃን ያጠናክራል። በዚህ ረገድ የባለሥልጣኑ ሃላፊነት በካፒታል ገበያ አዋጅ እና ለማስፈጸም በወጡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ እና የቁጥጥር መመሪያ፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ እና ለሕዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የገበያ ተዋንያንን የሥራ ሂደት መብት እና ግዴታቸውን በመለየት ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የእርምት እርምጃ መውሰድን ያካተተ ነው።

ገበያውም አባላቱን እና ግብይቱን ለማስተዳደር ባወጣው ውስጥ ደንብ መሰረት የዕለት ተዕለት በግብይት ሥራዎችን በመምራት እና በመቆጣጠር የሚፈጸሙ ጠፋቶችን በመመርመር እርምጃ መውሰዱ ለገበያው ተዓማኒነት እና ለኢንቨስተሮች በራስ መተማመን የራሱ አስተዋጾ አለው።

**የኢንቨስተሮች የፋይናንስ ግንዛቤ እና የባህሪ ክፍተቶች፡** ግዙፍ እና ቀጣይነት ያለው ብሔራዊ የፋይናንስ ግንዛቤ ዘመቻ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። በተጨማሪም ኢንቨስተሮች የጥበቃ ዘዴዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል። ለምሳሌ፣ የግምጃ ቤቱን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግለጫዎች እንዴት ማጣራት እንደሚቻል፣ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል እና የመሳሰሉትን

በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በሰፊው እየተሰራ ይገኛል፣ይሄው ተጠናክሮ ይቀጥላል።

**ቅንጅት እና የመረጃ ልውውጥ፡** በባለሥልጣኑ፣በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት እና በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ተቋማት መካከል ቀጣይነት ያለው ዘላቂ ትብብር ማድረግ ወሳኝ ነው። ይህም የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም በተቋማቱ መካከል ዘለቄታዊ የቅንጅት አሰራርን መዘርጋትን የሚያካትት ሲሆን ይሄው በተግባር እየተሰራበት የሚገኝ እና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው። በሃገር ውስጥ እና ውጪ ካሉ አቻ ተቋማት ጋር መደበኛ የትብብር ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና ወደ ተግባር መግባት ለኢንቨስተር ጥበቃ ለሚደረግ መረጃ ልውውጥ እና ለሌሎች የጋራ ስራዎች እጅግ አስፈላጊ ነው።

የካፒታል ገበያ ተቋማት ከሌሎች ሃገራት አቻ ተቋማት ጋር በጋራ በሚሰራባቸው ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ መጀመራቸው ጠቃሚ ነው። በዚህ ረገድ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ከታንዛንያ አቻው እና ሌሎች ሃገራት አቻዎች ጋር በጋራ ጉዳዮች በቅንጅት ለመስራት ንግግር ጀምረናል። በዚህም የመግባቢያ ስምምነቶች በማዘጋጀት የትብብር ማዕቀፍ መዘርጋት እና ምርጥ ተሞክሮዎችን መውሰድ ለሚደረገው የኢንቨስተር ጥበቃ እና ለገበያው እድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

**ባለብዙ መድረክ የኢንቨስተሮች እና የሚመለከታቸው አካላትን ትምህርት መስጠት፡** ስለ ካፒታል ገበያ እና የኢንቨስተር ጥበቃ መሳሪያዎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ ማህበራዊ ሚዲያ እና የትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ የኢንቨስተሩን እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ ማሳደግ ማዕቀፉን ለማጠናከር ይረዳል። ባለሥልጣኑም ሆነ ገበያው ለሚመለከታቸው የፌደራል እና ክልል ተቋማት እንዲሁም ለካፒታል ገበያ ተዋንያን የኢንቨስተር ጥበቃ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራቱ እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተደራሽነቱን በማስፋት የኢንቨስተር ጠበቃ ስራን ግንዛቤ በማስፋት ይደግፋል።

በዚህ ረገድ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሃገር ውስጥ ካሉ የፌደራል እና የክልል የፍትህ ተቋማት ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ ፍትህ ቢሮ፣ አቃብያን ህግ፣ ፖሊስ፣ ጸረ-ሙስና፣ የፋይናንስ ደህንነት እና ሌሎች መሰል ተቋማት የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህ የባለድርሻ አካላት የንቃተ ህግ ከመጨመር ባሻገር በዘርፉ ለሚፈጸሙ ጥፋቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ መርምሮ እልባት ለመስጠት በሚያስችል ቁመና እንዲገኙ የካፒታል ገበያ ህጎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳል።

## 5. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የኢንቨስተር ጥበቃ ተቋማዊ ማዕቀፍ ባለሥልጣኑን፣ ግምጃ ቤቱን፣ ገበያውን እና የካፒታል ገበያ ፍርድ ቤቱን የሚያካትት ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃዎች በጥንቃቄ የተነደፈ ነው። ሰው ሰራሽ የማጭበርበር ሥራዎች የስራዓቱ አደጋዎች ናቸው። እነዚህን ስጋቶች ለመከላከል ከፈቃድ አሰጣጥ ጀምሮ መመሪያዎችን በጥብቅ መተግበር፤ የኢንቨስተሮችን የካፒታል ገበያ ሀብት

ለይቶ መያዝ ብሎም በግብይት ወቅት ቅኝት በማድረግ በመጨረሻም ጥፋቶች ሲፈጸሙ ወደ ማስተካከያ እርምጃዎች በማምጣት ቅሬታዎች በራሱ ፍርድ ቤት የሚፈቱበት አሰራር ተዘርግቷል።

የኢንቨስተር ጥበቃ ሥነ-ምህዳር የመጨረሻ ተጠቃሚ ኢንቨስተሩ ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ነው ማለት ይቻላል። ፍትሃዊ፣ ንፁህ እና ቁጥጥር የሚደረግበት ገበያ መሆኑ መልካም ስም እና እምነት የሚጣልበት እንዲሆን የሚረዳ ሲሆን ይህም ሃገራችን ለልማቷ የሚያስፈልገውን የረጅም ጊዜ ካፒታል መሳብ ያስችላታል። ከላይ የተጠቀሱት ተቋማት በሙሉ ተቆጣጣሪ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን የፋይናንስ የወደፊት እጣ ፈንታ መሰረት አራማጆች ናቸው። ጥንቃቄ የተሞላበት ንቁ እና ውጤታማ አሠራራቸው ካፒታልን ወደ ኢንቨስትመንት የሚቀይር እውነተኛ አነቃቂ ይሆናል፣ ይህም የአገሪቱን የኢኮኖሚ ታሪክ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ያቀጣጥላል።